ሕልሜ የተሻለ ሁኔታ ነበረዎት። እኔም ይህን በማየቴ በጣም ተረጋጋሁ። ብፁዕ አባቴ! ስለ እርስዎ ሁኔታ የሚነግረን ሰው አልነበረም ብልዎት ያምኑኛል? ስለ እርስዎ የሰማነው፥ ከሁለት ቀናት በፊት በአባ አርቄሊደስ አማካይነት ነው።

፭) <u>ደግና ለዛኝ አባቴ</u>! በልባችን፣ በሕሊናችን፣ በጸሎታችን ሁሉ፥ ቀንም ሆነ ማታ ተለይተውን አያውቁም። እግዚአብሔር ስለ እኛና ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲል፤ እር ስዎን ደህና ያድርግልን። ዕድሜዎትን ለዘመናት ያርዝምልን። በወላዲተ አምላክ ምልጃ፣ በቅዱሳኑና በእርስዎ ጸሎት፤ እግዚአብሔር ጠላት ዲያብሎስን በእግ ርዎ ሥር ያስገዛልዎት። ሁሉም መነኰሳይያት እኔም ጭምር፤ ቡሩካን እጆች ዎን እንስማለን፤ በጸሎትዎ ያሳስቡልን።

አክባሪ ልጅዎት ኄራኒ መርቆሬዎስ።

<u>ምዕራፍ አራት</u>

<u>ድል ከነሡት ጻድቃን ጋር፥ በኣንድነት የመንዝ ክብር።</u>

«የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፥ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከ ታችሁ ምሰሉአቸው»፣ «ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል፤ አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል»፥ (ራእ.፳፩፥፯፣ ዕብ.፲፫፥፯)።

<u>በበሽታ የሚገኝ ጸጋ፦</u> «እርሱም፦ ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ። እንግዲህ የክ ርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ» እንዲል ቅዱስ መጽሐፍ፥ ክብርት እናታችን እማሆይ ኄራኒ፥ የድኅነት ወደብ ላይ ለመድረስ ሩጫዋን ሁሉ በገ ድል ፈጽማለች። ገድሏም ለክብር የሚያበቃ ሆኖላታል (፪ኛ ቆሮ.፲፪፥፱)። የምር እንግ ድነት ጊዜዋ እስኪያበቃ ድረስ፤ የልብ መሻቷ ይፈጸምላት ዘንድ፥ ራሷን ንፁሕ መሥ ዋዕት አድርጋ በማቅረብ፤ ዕለት ዕለት እንደ ጧፍ እያበራች፣ እንደ ሻማ እየቀለጠች ኖራ፣ ድል በመንሣት ሰማያዊ መንግሥቱን ወራሽ ሆነች።

ቅዱሳን መላእክቱም፥ ይህንን መሥዋዕት መልካም መዓዛ እንዳለው ዕጣን ተቀብለው፤ ወደ ሰማያዊው መንበር አደረሱላት። የጌቶች ጌታ፣ የነገሥታት ንጉሥ የሆነ፥ ፈጣሪኣችን ባወረሳት ክብርና ሞገስ ነፍሷን አጅበው አሳረጓት። «ስለዚህ በእግዚ አብሔር ዙፋን ፊት አሉ፥ ሌሊትም ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል፥ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእ ነርሱ ላይ ያድርባቸዋል። . . . በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፥ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም ዕንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል። . . . እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደ ዱም» እንዲል (ራእ.፯፥፲፭/፲፯፤ ፲፪፥፲፩)።

በምድር ተሸክማውና ተፈትና ያለፈችበት መስቀል፤ በሰማያት ደግሞ የሞገሷና የክብሯ መገለጫ ሆነላት። ይህም የመሸቷ እሳት ይነድበት የነበረ፥ የሰማዕትነት ክብር ነው። የእማሆይ ኄራኒ ክብርና በላይዋ ያደረ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፤ በአካል አብረዋት ላሉና በርቀት ሆነው ለሚያስቧት ብቻ ሳይሆን፥ በዝና ለሚያውቋት ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ምሥጢር የተገለጠበት ነው። እማሆይ ኄራኒ፥ በሕይወት ዘመናሃያ ሰባት ቀዶ ሕክምናዎችን አድርጋለች። በእነዚህ ሕክምናዎቿ ምክንያት፤ ምን ዐይነት ሕይወት እንዳሳለፈች ለማሳየት ጥቂቶቹን እናቀርባለን፦

፩) የመጀመሪያው ቀ.ሕ.፥ በጥር ወር ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. ያስወጣችው የጨጓራ ነቀርሳ ነው። ይህን ከማድረጓ በፊት፤ በበሽታው ለዓሥር ዓመታት ተሰቃይታለች። እንደ ሳይንሱ ከሆነ መንሥዔው የጾም ብዛትና ራስን ማጉስቈል ነው። በአጽዋማት ጊዜ፥ ለቀናት አትመገብም። ከቀናት በኋላም ቢሆን የምትመገበው፥ ደረቅ ዳቦ በጨው ወይም በአትክልት መረቅ ብቻ ነው። ይህ ጸጋ የተሰጣት፤ ለእኛ በዚህ ዘመን ላለን ክርስቲያኖች ትምህርት ይሆነን ዘንድ ነው። በዚህ ዘመን በእንዲህ ዐይነት ሕይወት ውስጥ ለመኖር የሚመኝም ሆነ የሚፈቅድ የለምና።

፪) ጨጓራዋ ከመታወኩ የተነሣ፥ ደም በጣም ስለሚያመነጭ ለሞት ያደረሳት ጊዜ ነበር። ቀ.ሕ. ለማድረግ የተገደደችውም በዚህ ምክንያት ነው። በዚህ ወቅት የሚበላም ሆነ የሚጠጣ ነገር መቅመስ አትችልም ነበር። ሐኪም ቤት ሆና፤ ቀ.ሕ. በመጠባበቅ ላይ ሳለች፥ እመቤታችን ተገልጣላት፤ ፈውሼሻለሁ ከዚህ በኋላ አያምሽም አለቻት። በእርግጥም ወዲያው ጤና ስለተሰማት በተኣምር ለመዳኗ እርግጠኛ ሆና ነበር።

ግሬስ የተባለው የዕለቱ ተረኛ ሐኪም ግን፥ ተሽሎኛል ብላ በመናገሯ ሲያስብ የነበረው፤ በእውነት ተሽሏት ሳይሆን፥ ሆን ብላ ከቀ.ሕ. ለማምለጥ ስትል፤ ጥርሷን ነክሳ ያልታመመች ለማስመሰል እንደ ሞከረች ነበር። ስለዚህ ያልሸውን ብትዪ ሥራው መሠራት አለበት ብሎ አስገደዳት። እርሷ ደግሞ በበኩሏ የእርሱን አባባል የተረዳችው፤ እግዚአብሔር በድንቅ ተኣምራቱ፥ ሃይማኖት የለሽ የሆነውን ሐኪም፤ ወደ ትክክለኛውና እውነተኛው መንገድ ለማምጣት የተጠቀመበት ልዩ ጥበቡ መሆኑን ነውና፤ ሐኪሙ የወደደውን እንዲያደርግ ፈቀደችለት። የሕክምና ባለ ሙያዎቹ፤ ለሥራ ዝግጁ ሆነው ሲቀርቡ፥ ምንም እንኳን ምልክቱን ከዚህ ቀደም ያሳዩትና የራጂ ውጤቱም፤ የነቀርሳ ታማሚ መሆኗን ያመለከተ ቢሆንም። በሰውነቷ ላይ በግምት ለዓሥርና ዐሥራ አምስት ቀናት የቆየ የሚመስል ምልክት (ጠባሳ) አገኙ። ዶ.ር ግሬስ፥ ካየው ሁሉ የተረዳውና አንድ እጅግ የተደመመበት ጉዳይ ቢኖር፤ በመፈወሷ መቶ በመቶ እርግጠኛ የሆነችው እናት፤ የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም ስትል ብቻ፤ ቀ.ሕ. ለማድረግ መስማማቷ ነው።

ይህ ተኣምር፥ እናት ኄራኒ ለሰው ያላትን ጥልቅ ፍቅርና ስለ ነፍሳቸው ድኅነት ስትል፤ ምንም ከማድረግ ቸል እንደማትል ያሳያል። ስለ ሌላ ሰው ድኅነት ሲሉ፥ መጸለይ፤ ወይም የራስን ሳያጎድሉ መርዳት አንድ ነገር ነው። መከራን በፍቅርና በትዕግሥት ተቀብሎና ራስን መሥዋዕት አድርጎ፣ የሌላውን ልብ ለመግዛት መትጋት ግን ታላቅ ቅድስና ነው። በዚህ መንገድ፥ ሃይማኖት የለሹ ሐኪም፤ ወደ እውነተኛው እምነት ተመለሰ፤ በእውነተኛው አምላክ እንደሚያምን መሰከረ። ውዷ እናት ኄራኒ እስከ ሕይወቷ ፍፃሜ ድረስ ባደረገቻቸው የሕክምና ጉዞዎችና ውጣ ውረዶች፤ ብዙ ኢ-አማንያንን በዚህ ሁኔታ ወደ እውነተኛዋ ሃይማኖት አምጥታለች።

፫) አንድ ጊዜም እንዲሁ፥ በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. በደረሰባት ከፍተኛ ሕመም ምክንያት፤ ማሕፀኗን ማስወጣት ነበረባት። በሌላ ጊዜ ደግሞ፥ በ፲፱፻፹፪ ዓ.ም. የቀኝ እግሯ ሊቆረጥ ባለ ጊዜ፥ ብዙ ተሰቃይታለች።

የቀኝ እግሯ አውራ ጣት ላይ ጥፍረ መጥምጥ ይዟት ነበር። በዚህ ምክንያት፥ ጥፍሯ ቦታውን ለቆ ወደ ሥጋዋ ውስጥ ስለ ገባ በቀ.ሕ. አስወጣችው። በዚህ ሕክምና ወቅት በተፈጠረ ስሕተት ምክንያት፥ ሰውነቷ ተቆጥቶ ቁስሉ በፍጥነት እየሰፋ መጥቶ፤ ሕመሙ ለሙሉ እግሯ ተረፋት። ሆኖም ግን ሐምሌ ፳፭ ቀን ማክሰኞ ዕለት፥ ፲፱፻፹፩ ዓ.ም.፤ እመቤታችንና አቡ ሰይፊን ተገልጠው በተኣምር ፈውሰዋታል። ዕለቱም የአቡ ሰይፊን ቅዳሴ ቤቱ የሚከበርበት ነበር።

፬) የ፲፱፻፹ዎቹ መጀመሪያ ደግሞ፥ በልብ ሕመም የተቸገረችበት ጊዜ ነው። ይህን ሕመሟን የሚከታተልላት ፐ.ር ፋይዝ ፋይቅ ጴጥሮስ ነበር። እርሱም የልብ ሕመም ከጀመራት ጊዜ አንሥቶ፤ እስከ ዕረፍቷ ድረስ ያለውን ሂደት መዝግቦ አስቀምጦታል። ለዓመታት ያሰቃያት የነበረውን የልቧን ችግር፤ በቅርበት ክትትል ለማድረግ ይችል ዘንድ፤ ከሓያት ሆስፒታል የልብ ሕመም ባለሙያዎች ጋር በመሆን፤ በሳምንት አንድ ቀን ወደ ገዳሙ እየሄዱ ይመረምሯታል። ከዚህም በተጨማሪ፥ ወዳጆቹ የሆኑ ዶክተሮች ተራ ገብተው፤ በየዕለቱ እየተመላለሱ በማየት ውጤቱን ይነግሩታል። በየዕለቱ ክትትል የሚያደርጉላት ዶክተሮች ዝርዝር የሚከተለው ነው፦

ሀ) ፕሮፌሰር ዋግሕ አል-አስዩቲ፤
ለ) ፕሮፌሰር አስማት አክላዲዮስ፤
ሐ) ፕሮፌሰር ማግዳ ጊዮርጊስ፤
መ) ፕሮፌሰር ማሕር ፉዓድ፤
ሠ) ፕሮፌሰር ሐኒ ኤድዋርድ፤
ረ) ዶክተር ሻኪር ፋራግ፤
ሰ) ዶክተር ሸሪፍ ሔልሚ፤
ሸ) ዶክተር ሔኒ እናያት፤
ቀ) ዶክተር አሽረፍ ሳሚ፤
በ) ዶክተር አይማን ሔኒን፤
ተ) ዶክተር ሐዝም አንዋር።

ፕሮፌሰር ፋይዝ ፋይቅ፥ «በወጣት ዕድሜዋ የስኳር በሽተኛ ስትሆን፤ በሰውነቷ ያለው የቅባት መጠንም ከፍተኛ ነበር። በዚህ ምክንያት፥ ደሟ ስለሚረጋ በኣግባቡ የመዘዋወር ዐቅም አልነበረውም። ካይሮ ሂልዮፖሊስ በሚገኘው ሆስፒታል

ተኝታ፤ የወቅቱ የቴክኖሎጂ ዐቅም በፈቀደው መጠን የሕክምና ክትትል ተደርጎላታል» ብሏል።

፭) ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. ለሕክምና ወደ አሜሪካ ሄደች። ፲፱፻፹ዎቹ ማለቂያ ላይ ጀምሮ፤ የቀኝ ባቷ ላይ በተፈጠረ፥ ውስጡ ውኃ የቋጠረ ዕብጠት ምክንያት በሚሰማት ሕመም፥ እንደ ልቧ ለመራመድ አልቻለችም። ከዓመት ወደ ዓመት በተሸጋገረች ቁጥር፥ የሰውነቷ ክብደት እየቀነሰ መጣ። በተደረገላት ምርመራ ችግሯ ነቀርሳ መሆኑ ታውቆ፤ ኬሞቴራፒ መከታተል ጀመረች።

በዚህ የክትትል ወቅት ደግሞ፤ በቂ ደም ወደ ልቧ ባለመተላለፉ ምክንያት፥ ይበልጥ የከፋ ችግር ገጠማት። የሕክምና ውጤቶች ሁሉ የሚጠቁሙት፤ ይህንኑ የደም ዝውውር ችግር ነበር። የልብ ቀዶ ሕክምና ማድረግ በማስፈለጉ፥ ሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. በፕ.ር ጳውሎስ ቴይለር አማካይነት ተደረገ። በስኳርና በሌሎች ሕመሞች መሰቃየቷ ባይቀርም፤ የልቧ ቀ.ሕ. ግን፥ በረድኤተ እግዚአብሔር በተሳካ ሁኔታ ተጠናቀቀ። ምንም እንኳን የስኳር ታማሚ የሆነና ኬሞቴራፒ የሚከታተል ሰው ቁስል፥ ቶሎ እንደማይድንለት ቢታወቅም፤ ጥቂት ቀደም ብሎ ትከታተል የነበረው ኬሞቴራፒ ያደረሰባት ተጽዕኖ አልነበረም። ይህ የተደረገላት የልብ ቀ.ሕ. በሂደቱ የተወሳሰበ ከመሆኑም ሌላ፥ በሕክምና ሳይንስ አስተማማኝነቱ ለዓሥር ዓመታት ብቻ ሲሆን፥ እማሆይ ኄራኒን ግን፤ ለብዙ ዘመናት ያለ ችግር አቆይቷታል።

ከልብ ሕመሟ እያገገመች ባለችበት ጊዜ፤ እግሯ ላይ የተከሰተውን ዕብጠት ለማስወገድ የራዲዮቴራፒ ክትትል ጀመረች። ይህ ክትትል ውጤት ማምጣቱን ለመረዳት የ«CT Scn» ምርመራ ስታደርግ፥ ነቀርሳው ይብስ ተሰራጭቶ በመገኘቱ፤ ረጅም ጊዜ የሚወስድ የኬሞቴራፒ ክትትል እንደገና አስፈለጋት።

፮) በመስከረም ወር ፲፱፻፹፮ ዓ.ም.፥ ለዚሁ ሕክምና ሲባል ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አሜሪካ ሄደች። ሐኪሞቹም የዚህን ሕክምና የጎንዮሽ ጉዳት ልትቋቋም ስለመቻሏ እርግጠኞች አልነበሩም። ይህን ጥርጣሬ ያሳደረባቸው ደግሞ፥ ንጹሕ አየር የሚያመላልሰው ቀይ የደም ሴሏ ማነሱ፤ የስኳር ሕመምተኛ መሆኗና የልቧ ችግር ነው። እንደ ተፈራውም ሙከራው የልቧን ጡንቻዎች ጎድቶባታል።

ዘግይተው ባደረጉላት ምርመራ ደግሞ፥ ምንም ዐይነት የነቀርሳ ምልክት በአካሏ ላይ ማግኘት አልቻሉም። የዚህ በሽታ ልዩ ባለሙያ የሆነው ሐኪሟ፥ በመጨረሻ ይህ በገሓዱ ዓለም የተከሰተ ተአምር እንጂ፥ ሌላ ነገር ሊሆን አይችልም ብሎ፥ ከሙያዊ አስተሳሰብ ውጭ የሆነ ምስክርነቱን ሰጥቷል። ይህ ተአምር ኢ-አማኒ (ከሃዲ) የነበረውን ሐኪም፤ በእውነተኛው አምላክ እንዲያምን አስገድዶታል።

እማሆይ ኄራኒም የወርቅ መስቀል ሰጥታዋለች።

፯) በመስከረም ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.፥ እንዲሁ ልቧን በመታመሟና ምግብም ስለማይረጋላት፥ ወደ ሕክምና ሄደች። የምትወስዳቸው መድኃኒቶች ለውጥ ባለማምጣታቸው፥ በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ወደ አሜሪካ ተመልሳ መሄድ ነበረባት። ዶ.ር ኮራንድ ባደረገላት ምርመራ፥ የልቧ ደም ሥሮች በአደገኛ ሁኔታ መጥበባቸውን ተናገረ። ከዚህ በመነሣት ባለሙያዎቹ፥ ቀሪ ዘመኗ ስድስት ወራት ብቻ መሆናቸውን ነግረው፤ የሌላ ሰው ልብ እንዲቀየርላት ሐሳብ አቀረቡ። እርሷ ግን ሐሳቡን ባለመቀበሏ፥ ሌላው አማራጭ፤ ልቧ ሥራውን ፈጽሞ እስኪያቆም ድረስ መጠበቅ ብቻ ነበር።

፰) በሰኔ ወር ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.፥ እንደገና ወደ አሜሪካ ሄዳ ስትታይ፤ ችግሩ እጅግ ብሶ አገኙት (ድሮውንም እነርሱ እስካሁን ትቆያለች የሚል ግምት አልነበራቸውም)። ዶ.ር ጀምስ ያንግ፥ ከዚህ በኋላ ቀ.ሕ. ማድረግ ምንም እንደማይፈይድ ገለጸላት። የምትወስደው መድኃኒትም ቢሆን ተስፋ የሚጣልበት ባይሆንም፤ ሌላ አማራጭ ባለመኖሩ እሱኑ እየወሰደች ፍጻሜዋን እንድትጠብቅ በሚል አስተሳሰብ ነው። በሰዎች ዘንድ አለቀላት ቢባልም፤ እግዚአብሔር ደግሞ የተቈረጠውን ይቀጥላልና፤ በዚያው ባለችበት የጤንነት ሁኔታ፥ ለዓመታት አቆይቷታል።

፱) አሁንም በዚሁ ከባድ የልብ ሕመም ምክንያት፥ በ፲፱፻፺፬ ማለቂያ ላይ፥ ካይሮ አል-ሐያት ሆስፒታል ገባች። የልብ ደም ሥሮቿን በመታከም ላይ ሳለች፥ ሕመሟ እየተባባሰ መጥቶ በተደጋጋሚ ጊዜ የልቧን ምት እስከ ማቆም አድርሶት ነበር። በዚህ ምክንያት አጣዳፊ የልብ ሕመም (የልብ ምት ማቆም) ለገጠማቸው ሰዎች የሚደረገው የልብ ማነቃቂያ የኤሌክትሪክ ሕክምና (Electric Cardiac Shok) ለአርባ አምስት ደቂቃዎች መከታተልና ሰው ሠራሽ መተንፈሻ መጠቀም የግድ አስፈላጊዋ ሆኖ ነበር። በተደጋጋሚ ጊዜ ራሷን እየሳተች ስለምትቆይ፥ በፕ.ር ፋይዝ ፋይቅ አማካይነት ረዘም ላለ ጊዜ የሚያገለግል የልቧን ምት ማስተካከያ ቱቦ ተደረገላት።

በዚህ ሂደት ውስጥ ለሁለት ቀናት ራሷን ሳታውቅ ከቆየች በኋላ፥ ቀስ በቀስ መንቃት ጀመረች፤ የጤንተቷ ሁኔታም መሻሻል አሳየ። ነገር ግን ብዙም ሳትቆይ፥ የልቧ ሕመም እንደገና በአስከፊ ሁኔታ ጀመራትና፤ ምንም ዐይነት ሕክምናም ሆነ መድኃኒት የማይረዳት ደረጃ ላይ ደረሰች። አሁንም ሌላ የልብ ምት ማስተካከያ ቱቦ መጠቀም አስፈላጊ ቢሆንም፥ ቀደም ብሎ በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. አሜሪካ በነበረች ጊዜ ባደረገችው ሕክምና፥ ልቧ ውስጥ በተደረገላት ቱቦ ምክንያት፤ ሁኔታው እጅግ ስለተወሳሰበ አሁን ተመሳሳይ ሕክምና ማድረግ እጅግ አስቸጋሪ ሆነ።

ቀደም ተብሎ ተነግሯት እንደ ነበረው ሁሉ፥ በችግሮቹ ውስብስብነት ምክንያት ምንም ማድረግ እማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደረሰ። ክብርና ምስጋና ሁሉም

ለእርሱና ለወዳጆቹ ይሁንና፤ እግዚአብሔር ግን ፈቃዱን የሚፈጽምበትና ሥራውን የሚሠራበት መንገድ፤ ከሰዎች ዕውቀትም ሆነ ከሕክምና ጥበብ በላይ ነውና ለጥቂት ጊዜ ጤንነቷ ተመልሶ ሰላሟን አገኘች።

፲) ታኅሣሥ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም.፥ በዚያው ሆስፒታል ውስጥ ከበፊቱ ተመሳሳይ የሆነ ውስብስብ የልብ ሕክምና ተደረገላት። ሕክምናውን ሲያደርግላት የነበረው፤ በዚያን ጊዜ በአጋጣሚ ግብፅ ውስጥ የነበረ ዶ.ር ዳዊት ፎሊ ነው። ባደረጋቸው ሙከራዎች ሁሉ፥ የልቧ ደም ሥሮች ይበልጥ እየጠበቡና አስጊ እየሆኑ በመምጣታቸው፤ የዶክተሩ የመጨረሻ ቃል «ስላልተሳካልን ቤተሰቧ ይህን ይረዳልን ዘንድ እናሳስባለን» የሚል ነበር።

ዶ.ር ፎሊ እናት ኄራኒን ከዚህ በፊት አያውቃትም። በተኣምርም የሚያምን ሰው አልነበረም። በዚሁ በልቧ ችግር ምክንያት፤ በጀርባዋ ተንጋልላ ከጥቂት ደቂቃዎች በላይ መቆየት ስለማትችል፤ የደም ሥሮቿን ክፍተት ለማስፋት የተኪያሄደው ሕክምና፤ በተቻለ መጠን በፍጥነት ነበር የሚሠራው። ምንም እንኳን እነርሱ ራሳቸው፥ በሰው ሰውኛው ዐቅማቸው፤ ፈጣን ሥራ ለመሥራት ያቀዱ ቢሆንም፥ ረዥም ጊዜ የሚጠይቀው ሕክምና፤ ግማሽ ሰዓት ሳይሞላ ተጠናቀቀ።

ይህ ፍጥነት ያስደነቀው ዶክተር፤ ረዳቱ የሆነው ዶ.ር ሐዝም አንዋርን፥ ሴትየዋ ማናት? ብሎ ጠይቋል። ራሱም በዓይኖቹ ያያቸው ብዙ ምልክቶች ስለ ነበሩ፤ ማንነቷ ሲነገረው፥ በተኣምረ እግዚአብሔር ማመን ግድ ሆነበት። ስለዚህ በየዕለቱ እየመጣ፤ ሁኔታዋን መከታተል ጀመረ። በዚህ ጊዜ ያበረከተችለት መስቀል እስካሁን ድረስ አብሮት አለ። እርሷን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕረፍቷ ድረስ «ቅድስቷ እናታችን እንዴት ናት?» እያለ ይጠይቅ ነበር።

፲፩) ከሐኪም ቤት ከወጣች በኋላ፥ አድካሚ ሥራዎችን እንድትቀንስ ቢነገራትም፥ ተፈጻሚ ባለማድረጓ፤ በየጊዜው ወደ ሐኪም ቤት ተመላለሳለች። ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. በጣም ታማብን ይዘናት ሄድን። ለተለመደው ሕክምና ቅድመ ዝግጅት ላይ ሳሉ፥ ሐኪሙ ሙሉ ጤነኛ መሆኗን ተናገረ። ከዚህ በኋላ ይበልጥ የመጠንከር ለውጥ አመጣች። ሆኖም ግን አልፎ አልፎ ወደ ሐኪም ቤት ከመወሰድ አልዳነችም። ሕክምናው ሲደረግላት ደግሞ፤ ከሐኪሞቹ መረዳት በላይ በሆነ መንገድ፥ ይሻላትና ትመለሳለች። ወደ አሜሪካ ስትሄድም፤ የቀድሞ ሐኪሟ፥ መምጣቷን ሲሰማ፥ ተደንቆ እስከ ዛሬ በሕይወት አለች እንዴ? ብሎ ነበር። ይህን ያለበት ምክንያት፥ የእርሷ ዐይነት ችግር ያለበትን ሰው ለማዳን፤ የሕክምና ሳይንስ ዐቅም ስለሌለው መሆኑንም ገለጸልን።

፲፪) ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ሐያት ሆስፒታል በተወሰደች ጊዜ፥ ልቧ እጅግ ደክሞ

ነበር። ለዚህኛው ችግር ያጋለጣት በነሐሴ ወር ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. ለሚውለው የአቡታት የስኳር ሕመምተኛ በመሆኗ ምክንያት፥ በቀን ሁለት ጊዜ መርፌ ትወጋ ለች። እንዲሁም ሽንት የሚያሸና ፈሳሽ መድኃኒት በብዛት ትወስዳለች። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን፥ ኩላሊቷ ጤነኛ ነበር።

፲፫) ጥቅምት ፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በሕክምና ላይ ሳለች፥ ከአልጋዋ ላይ ወድቃ የቀኝ እግሯ ዐጥንት ስለ ተሰነጠቀ፥ እግሯ በጀሶ ታሠረላት። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኩላሊቷን ከጥቅም ውጪ የሚያደርግና፣ በማንኛውም ሰዓት የልቧን ምት ለማስቆም ሚያስችል አስጊ ችግር ተከሰተ። ፕ.ር ማሕር ፉዓድ ራምዚና ፕ.ር ሔኒ ኤድዋርድ ያሳ፥ ከፍተኛ ክትትልና ሕክምና ቢያደርጉላትም ውጤቱ ለውጥ አልነበረውም። በመጨረሻ ምንም ዐይነት ሕክምናም ሆነ መሣሪያ ሊረዳት ባለመቻሉ፥ የልቧ ምት አቆመ። ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ከዚች ዓለም የእንግድነት ኑሮ አረፈች።

በሕክምና ሳይንስ እንደሚነገረው፤ የልብ ጡንቻ የመሥራት ዐቅሙ 15% የደረሰና፥ እንደ እናት ኄራኒ በሌሎች ተጨማሪ በሽታዎች የሚሰቃይ ሰው፤ ዕድሜው በጣም አጭር ነው። በተለይ ደግሞ አሜሪካ በነበረችበት ጊዜ፥ ከተደረገላት እጅግ የተወሳሰበና አደገኛ ሙከራ በኋላ፤ በእነርሱ ስሌት ከስድስት ወራት በላይ አትቆዩም ቢሏትም፤ የእርሷ ዕድሜ የተሰፈረው በምድራውያን ሥጋውያን ጠበብት ሳይሆን፤ የጠቢባን ጠቢብ በሆነ፥ ጥበብን ለሁሉ በሰጠ በሰማያዊ አምላክ በመሆኑ፥ ከነሕመሟም ቢሆን ለዘመናት ኖራለች።

የምድራዊ (እንግድነት) ጉዞዋ ፍጻሜ፦ እናታችን የሥጋ (ምድራዊ) የዕረፍት ጊዜዋ እንደ ቀረበ፤ ብዙ ምልክቶች ተስተውለው ነበር። ለምሳሌ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ሐኪም ቤት ስትወሰድ፥ ሁላችንንም ተሰናበተችን። እኛ እውነት ነው ብለን ባንቀበለውም፤ መኪናው ውስጥ እስከገባችበት ጊዜ ድረስ፥ እጆቿን እያውለበለበች፤ በቃ! መሄጃዬ ደርሷል፣ ከአሁን በኋላ የጥቂት ቀናት ጉዳይ ነው፣ ይኸው ነው እንግዲህ! ወደ ሰማያዊ አባቴ መሄዴ ነው፥ ብላን ነበር። ሐኪም ቤት ተኝታም ቢሆን፥ ያለማቋረጥ «ይቺን ዓለም ልለያት ነው፣ ወደዚህ የሕክምና ማዕከልም ካሁን በኋላ አልመጣም» ብላናለች። ለሐኪሞቿም መጪውን ኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. የአቡ ሰይፊንን በዓለ ንግሥ፥ በሰማይ ሆኜ ነው የማከብረው ብላ በእርግጠኝነት ከመንገሯም ሌላ፤ በታላቅ ፍቅር ትረዳትና ትንከባከባት የነበረችውን ረዳት ሐኪም «ከዕረፍቴ ጥቂት ቀደም ብዬ፥ እወድቃለሁ እግሬም ይሰበራል» ብላት ነበር። ይህም ተፈጽሞ ተመልክተናል።

የሕይወቷ ፍጻሜ ደርሶ፥ በዚህ ሁሉ ከሐኪሞች ችሎታ በላይ በሆነ የጤና እጦት ላይ ሆና እየተሰቃየች፤ ወደ እግዚአብሔር መጸለይዋንና ማመስገኗን አላቋረ

ጠችም:: ለእኛም የሰማዕትነት ክብር እንደምታገኝ ነግራ፥ በጸሎት አስቡኝ ትለን ነበር::

<u>ከዘወትር ጸሎቷ ጥቂቱ የሚከተለው ነው፦</u>

✝ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ! የአምላካችን እናት፣ የሰላምና የፍቅር እናት፥ ተወዳጁ ልጅሽ ጸሎቴን ይሰማኝና ይቀበለኝ ዘንድ ለምኚልኝ!

✝ አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ኀይልንና ብርታትን ስጠኝ:: አቤቱ ጌታዬ ሆይ! እርዳኝ! አቤቱ በቸርነትህ አስበኝ!

✝ አቤቱ አምላኬ ሆይ! ከዚች ዓለም ከመለየቴ በፊት፥ ለንስሐ አብቃኝ! ወደ አንተ ከመጠራቴ በፊት ኀጢአቴን ለመናዘዝ ፈቃድህ ይሁንልኝ!

✝ ጌታዬና መድኃኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! አመሰግንሃለሁ:: ጌታዬና መድኃኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! አከብርሃለሁ:: . . . የፍቅር አምላክ ሆይ አመሰግንሃለሁ::

✝ የሕመሜ ስቃይ ከእኔ ዐቅም በላይ መሆኑን አንተ ታውቃለህ:: ሰማዕትነት እየተቀበልሁ ነው፣ በሰማዕትነት እየሞትሁ ነውና አንተ እርዳኝ፣ ኀይልም ሁነኝ::!

ሰኞ ዕለት ጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ሁለት ጊዜ የልቧ ምት ቆሞ ወደ ጽኑ ሕሙማን መታከሚያ ተወስዳ ነበር:: ምንም እንኳን ለእኛ ግልጽ የሆነልን ከዕረፍቷ በኋላ ቢሆንም፥ የሚመጣውን ኀዘን ለመቋቋም ራሳችንን እንድናዘጋጅ፤ እግዚአብሔር አሳስቦናል (ምልክቶችን አሳይቶናል)::

በዚህ ዕለት ጥቅምት ፳ ቀን የተነበበው ወንጌልም፥ አምስት፣ ሁለትና አንድ መክሊት ከጌታቸው ስለተቀበሉት ባሮች የሚያስተምረው፤ በቅንነት በመክሊቱ አትርፎ የመጣው በታማኝነት ሲሾም፤ መክሊቱን ቀብሮ አቆይቶ ያለትርፍ የመለሰው ግን፥ ያለውንም ተቀምቶ በብዙ ላተረፈው ተጨመረለት፤ እርሱ ግን ወደ ጨለማ ተጣለ:: የሚለው ማቴዎስ ፳፭፥፲፬-፴ ላይ ያለው ጥቅስ ነው:: በጌታው የታመነውና በመክሊቱ የተጠቀመው አትራፊ እንደሆነው ሁሉ፥ እናታችን ኄራኒ ለዚህ ካልተገባች ማን ብቁ ሊሆን ነው? «ካህናቶችህ ጽድቅን ይልበሱ፥ ቅዱሳንህም ደስ ይበላቸው» (መዝ.፻፴፩፥ ፱):: «የእግዚአብሔርን ቃል የነገሩአችሁን መምህሮቻችሁን አስቡ፤ መልካም ጠባያቸውን አይታችሁ በእምነት ምሰሉአቸው:: . . . ስለዚህም ኢየሱስ ሕዝቡን በደሙ ይቀድሳቸው ዘንድ ከከተማ ውጭ ተሰቀለ:: አሁንም ተግዳሮቱን ተሸክመን፥ ወደ እርሱ ወደ ከተማው ውጭ እንውጣ:: . . . ለመምህሮቻችሁ ታዘዙ፤ ተገዙላቸውም፤ ስለ እናንተ በእግዚአብሔር ፊት ምላሽ የሚሰጡ እንደ መሆናቸው፥ ይህን ሳያዝኑ ደስ ብሎአቸው ያደርጉት ዘንድ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉና»፥ (ዕብ.፲፫፥፯፣ ፲፪፣ ፲፫፣ ፲፯)::

በዕለቱ የሚነበበው ስንክሳርም፥ ስለ አንድ በቅድስናው ስለታወቀ አበምኔት ያወሳል:: እርሱም ታላቁ ባሕታዊ ዮሐንስ ቆሎቦስ (Colobos) (ቅዱስ ዮሐንስ ሐጺር

ነው) (፫፻፴፪-፬፻፪):: የዕለቱን ምንባባት ሁሉ የእርሷን ክብር ገላጭ ሆነው አግኝተናቸዋል:: ይህ ሁኔታ እያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ዘልቆ በመግባቱ፥ በሥርዓተ ቅዳሴው ላይ በቦታው የነበረ ሁሉ ከልብ አልቅሷል::

<u>ሥጋዊ ዕረፍት፥ ዘለዓለማዊና ሰማያዊ ሕይወት</u>፦ የእናት ኄራኒ ነፍስ ከሥጋዋ የተለየችው፥ ማክሰኞ ዕለት ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ከቀኑ በ፲፪ ሰዓት ነው:: ይህም በቅብጥ ቤተ ክርስቲያን አቈጣጠር፥ ወር በገባ በሃያ አንደኛው ቀን፤ የእመቤታችን ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም በዓል የሚከበርበት ነው:: በዚሁ ዕለት የዓልአዛር ፍልሰተ ዐፅሙ፣ የነቢይ ኢዩኤልና የቅዱስ ሩዊስ የዕረፍታቸው መታሰቢያ በዓል ነው::

ብፁዕ አባታችን አንባ አርሳንዮስ የሜንያና የአቡ ቆርቃስ ሀ.ስ. መጢሮሊጥ[18]፤ እናት ኄራኒ «ኮማ» ውስጥ በነበረችበት ጊዜ፥ አይቷት ነበር:: ለሕሙማን የሚጸለየውንና የንስሐ ጸሎት እንዳደረሰላት፥ እማሆይ ኄራኒ፥ «ጌታዬ! አሁን ባርያህን በሰላም አሰናብታት» ስትል አደመጠ:: ከንግግሯ፥ ፍጻሜዋ መሆኑን የተረዳው አቡን ከአጠገቧ ዘወር ብሎ አለቀሰ:: ማታ አራት ሰዓት ላይ፥ ቅዱስ ሥጋዋን ይዘን ወደ ገዳም ተመለስን:: ይህን ድንገተኛ ኀዘን የሰማ የከተማዋ ክርስቲያን ወዲያው ወደ አ.ሰ.ሴ.ገ. በመጉረፉ ሌሊቱን ሙሉ፥ የገዳሙን በር መዝጋት አልቻልንም:: መነኮሳይያቱ በሙሉ ከአካሏ አጠገብ ሳንርቅ፥ ተሰባስበን የሌሊትና የነግህ ጸሎት አደረስን፣ ዳዊት ደገምን:: በመጨረሻም ረቡዕ ዕለት፥ ጥቅምት ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. እንዲሁ ከሥጋዋ አጠገብ ሳንርቅ ሥርዓተ ቅዳሴውን ተከታተልን::

<u>እናታችን ኄራኒ በእኛ ዘንድ ያሳት ሥፍራ</u>፦ ረቡዕ ዕለት የሚያውቋት ሁሉ፥ ከግብፅም ከውጭ ሀገራትም፤ የመጨረሻ ስንብት ሊያደርጉ፣ አክብሮትና ፍቅራቸውንም ለመግለጽ መጡ:: በዚያን ጊዜ የነበረውን ሁኔታ፥ አንዳንድ ጋዜጦች ባቀረቡት ዘገባ <u>የሕዝብ ጎርፍ</u> ብለውታል::

እናት ኄራኒን የሚያውቋት ብቻ ሳይሆኑ፤ የቅድስናዋን ዝና የሰሙ ሁሉ፥ የተሰማቸውን ኀዘን ለመግለጽ ይጎርፉ ስለ ነበር፥ በዕለተ ረቡዕ፤ በሌሊትም ሆነ በቀን የገዳሙን በር መዝጋት የማይታሰብ ነበር:: በየተራ እየገቡ ከቅዱስ ሥጋዋ ቡራኬ ለማግኘት፤ ለሰዓታት የሚያስጠብቅ ወረፋ መያዝ ለእነርሱ አስልቺ አልነበረም:: ከባድራን ደሴት፥ ከቅዱስ ጊዮርጊስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የመጣው ጊዮርጊስ ፋትሒ፤ ለሦስት ሰዓታት ወረፋ ጠብቆ፤ ገብቶ ከተሰናበተና በረከቷን ካገኘ በኋላ፥ «ምንም እንኳን ወገቤን ታማሚ ብሆንም፥ ለዓሥር ሰዓታትም ቢሆን ቆሜ ተራዬን እጠብቅ ነበር» ብሎናል:: የሰባ ዓመት እናቱም እንዲሁ፥ ያለ መታከት ተሰልፋ ነበር::

---

18 {የአንድ ሀገረ ስብከት ጳጳስ (መጽሐፈ ምሥጢር/ ትርጒም በመ/ር ኀይለ ማርያም ላቀው፤ ገጽ ፪፸፩::}

እል ማሻኺር የተሰኘ ጋዜጣ፥ ስለዚህ ዕለት ሲጽፍ የተባረከና የእምነት ኀርፍ የታየበት ቀን ነበር። ቅዱስ ሥጋዋ በእግዚአብሔር ሰላም ባረፈው እናት ዙሪያ የተሰበሰበው ሕዝብ፤ ትሕትናውና ተመስጦው ልዩ ነበር። መልአካዊ ፊቷን ላየ ሰው፤ በሰላምና በፈገግታ ውስጥ፥ ጊዜያዊ ዕንቅልፍ የተኛች እንጂ፤ ለዘላለሙ ያሸለበች አትመስልም፥ ብሎ ዘግቧል። በእርግጥም ፈገግታ የተላበሰውን ገጽታዋን ላስተዋለ ሰው፤ የእግዚአብሔርን መላእክት መስላ ትታይ ነበር።

ሰማያዊት ሙሽራ፦ ለዚህ ሰርግ ወይም ለሰማያዊ ሙሽርነት መታጨት የሚችል ሰው፤ ያለ ምንም ማስመሰያ፣ ማሻሻያና ማስተካከያ ፈጣሪውን በሙሉና በንጹሕ ልብ የሚወድ፣ የሚገዛለትና የሚታዘዘው ብቻ ነው። በዚህ መንገድ፥ ያለ መሰናክል ለማለፍ የቻለ ብፁዕ ነው። የንጹሕ በግ ሙሽራ ለመሆን ታድሏልና። ሰማያውያን መላእክትም፥ በታላቅ ደስታ ይጠብቁታል፣ ይቀበሉታል፣ ያከብሩታል።

እኩለ ሌሊት ላይ፥ መነኮሳይያት እኅቶቿ ቅዱስ ሥጋዋን ተሸክመው፤ በገዳሙ ወደሚገኘው የቅ.ማ.ቤ.ክ. አደረሱ። ሌሊቱንም ከአካሏ ሳይለዩ በጸሎት አሳለፉ። ኀሙስ ዕለት ጥቅምት ፳፪ ቀን በነግህ ጊዜ፤ ካህናቱ ተሰባስበው፤ ለዕለቱ ተገቢ የሆነው ሥርዓተ ጸሎት ተፈጸመ። በዚህ ጊዜ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኖዳ ሣልሳይ፥ አሜሪካ ውስጥ፥ የጀርባ ዐጥንት ቀዶ ሕክምና እየተደረገለት ስለ ነበር፤ ከእኛ ጋር ሊገኝ አልቻለም። የእርሱ ረዳት የሆነው ብፁዕ አባ ሩዊስ፣ የሜ.እ.ቆ.ሀ.ስ. መጢሮቦሊጥ ብፁዕ አባ አርሳንዮስ፣ የበርሚንግሃም ሀ.ስ.ሊ.ጳ. ብፁዕ አባ ሚካኤልና የብራዚል ሀ.ስ.ሊ.ጳ. ብፁዕ አባ አጋቶን በሥርዓቱ ላይ ተገኝተዋል።

ከቅዳሴ በኋላ አራት ሰዓት ላይ፤ ዐሥራ አንድ ብፁዓን ሊ.ጳ.፣ የየገዳማቱ አበምኔቶችና እመምኔቶች፣ እጅግ ብዙ መነኮሳትና መነኮሳይያት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት፣ ተገኝተው ለሁለት ሰዓታት ጸሎት ሲያደርሱ ቆዩ። እንዲሁም ወ.ሮ ፋውዚ ሳኮር -ከፖሊት ቢሮ ክቡር ፕሬዚደንት ሞሐመድ ሆስኒ ሙባረክን፣ ጀኔራል ሲድሆም -የሃገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስቴርን፣ መሐንዲስ ማግድ ጊዮርጊስ -የአካባቢ ጥበቃ ሚንስቴርን ወክለው፥ በሥርዓተ ቀብሩ ላይ ተገኝተዋል።

የብፁዕ አቡነ ሩፋኤል ቃለ ምእዳን፦ የቤተ ክርስቲያናችን አባት፤ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ሲኖዳ ፫ኛንና ሌሎች በሥርዓተ ቀብሩ ላይ የተገኙና ያልተገኙ ብፁዓን አባቶችን ወክዬ እዚህ ተገኝቻለሁ። በቅብጥ ቤተ ክርስቲያን የእ.ሰ.ሴ.ገ. እመምኔት የነበረችውን፥ የእናት ኄራኒን የመጨረሻ ስንብት፥ በዛሬው ዕለት እናደርጋለን። በዚህ ሰዓት እናታችን ኄራኒ፥ በእግዚአብሔር እጅ የክብር አክሊል የተቀዳጀች መሆኑ አያጠራጥረንም።፤ ይህም፦

፩ኛ) በድንግልናዋ ያምታገኘው አክሊል፦ በሰኞው ውዳሴ «እናንተ ደናግል! ንጽሕናን

ውደዱ! የድንግል ማርያም ልጆች ትሆኑ ዘንድ» እንደተባለ፥ በንጽሕና፣ በድንግልናና በምንኵስና ኖራለችና የቅድስት ድንግል ማርያም እውነተኛ ልጅ ትባላለች። እንደ ቅድስት ዴምያናና አርባው ደናግል ትቈጠራለች። ለብዙዎች መልካም እናት ነበረችና። በእሑድ ውዳሴ ማርያም ላይ፥ «በቅድስናሽ ምክንያት፥ በአንቺ በኩል ብዙዎች ወደ እግዚአብሔር ይቀርባሉና» እንደምንል ሁሉ።

ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ለአገልግሎት ወጣች፣ ወይም እንደ ሐዋርያት ለስብከተ ወንጌል ተሰማራች ሲባል አልሰማንም። ነገር ግን በድንግልና ሕይወቷ፣ በትሕትናዋ፣ በንጽሕናዋና ቅድስናዋ ለብዙዎቻችን አርኣያ ሆናለች። በቅድስናዋ ባገኘችው የአምላክ እናትነት፥ በተሰጣት ሥልጣን፤ ብዙዎችን ለእግዚአብሔር መንግሥት አብቅታለች፣ ታበቃለችም። ይህንን አባባል ከእመቤታችን ቀጥሎ፥ ለሰው ዐቅም እንደሚመጥነው ልክ ለእናት ኄራኒ ልደግመው እሻለሁ። ምክንያቱም እርሷም በሰማያዊት እናቷ አርኣያነት፥ በምንኵስና ሕይወቷ ብዙዎችን ለመንግሥተ እግዚአብሔር አብቅታለችና።

፪ኛ) በገድል የምታገኘው አክሊል፦ የድንግልና ጸጋ እንዲህ በቀላሉ የምትገኝ አይደለችም። ምክንያቱም ንጽሕናን የሚሹትን ሁሉ፤ ጸላኢ ዝም ብሎ አያያቸውምና፥ ጽኑ ተጋድሎ ይጠበቅባቸዋል። ፈታኙ ሁሌም እነርሱን በኃጢአት ለመጣልና ከንጽሕና ክብራቸው ዝቅ ለማድረግ ይተጋልና። ይህን ፈተና አሸንፈው ለድንግልና ክብር የሚበቁ ንዑዳን ክቡራን ናቸው። ስለ ጽኑ ገድላቸው የክብር አክሊልን ያገኛሉና።

የእናት ኄራኒ ገድል ደግሞ መንፈሳዊ ብቻ አልነበረም። በበሽታ ዐይነቶች ሁሉ የተጎዳው ሥጋዋም፤ ታላቅ ገድልን ይጠብቅባት ነበር እንጂ። በጠንካራ መነኵሲትነቷ ይህን ሁሉ ፈተና ተቋቍማ ኖራለች። ስለዚህ፥ የድል ባለቤትነቷ፤ በሥጋዊም በመንፈሳዊም ብርታቷ ነው። እንደ ገዳም አስተዳዳሪነቷም ብዙ ፈተናዎችን ተቋቁማለች። የድንግልና፣ የበሽታ፣ የአስተዳደራዊ አገልግሎት ፈተናዎችን ማለፏ ብቻ ሳይሆን፥ አስተዳደሯ መልካም መሆኑም በራሱ ዋጋ አለው። ከዚህ ገዳም ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ፤ ብዙ ብዙ ደክማለች። የገዳማውያኑ መንፈሳዊ ዕድገትና የራሱ የገዳሙ መሠረታዊ ለውጦች፣ የሥራዎቹ ብዛት፥ ለዚህ ልፋቷ የሚታዩ፣ የሚዳሰሱ ምስክሮች ናቸው።

በእናትነቷ የሚኰሩትና የሚደሰቱት፤ የዚህ ገዳም መነኵሳይያት ብቻ ሳይሆኑ፤ ከገዳሙ ውጪ ያሉ ክርስቲያኖች፣ እንዲሁም በሃገሪቱ ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ፥ በውጪ ሀገራት ያሉትም ጭምር መሆናቸውን ሁላችንም እናውቃለን። በየቦታው በምክሯና በጸሎቷ የሚጽናኑ፣ የሚወዷትና የሚያከብሯት፥ ብዙ የመንፈስ ልጆችና ወዳጆች አሏት። የምእመናንን ብቻ ሳይሆን የሊቃነ ጳጳሳቱን፣ የቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን ልብ መግዛት የቻለች እናት ናት። ስለዚህ እናታችን በነ

ዚህ ሁሉ አገልግሎቶቿና ገድሎቿ የክብር ባለቤት ናት::

በዚህ ሰዓት እኛ የሥጋ ሽኝት ስናደርግላት፤ ነፍሷ ደግሞ፥ በሰማያት በታላቅ ክብር ከተቀበሏት፥ ከመላእክትና ከጻድቃን ጋር የዝማሬ ተካፋይ ሆና ሐሴት ታደርጋለች:: «መዓዛዋም እንደ ከርቤና እንደ ዕጣን የሆነው፥ ከልዩ የሽቱ ቅመም ሁሉ የሆነው፥ ይህች ከምድረ በዳ እንደ ጢስ ዐምድ የወጣችው ማናት?» እንዲል (መኃ.፫፥፮)::

እርሷ በበረኻ ከተመሰለችው ምድር፤ ወደ ሰማያዊ መንግሥት ሄዳለች:: በአንድ ብቻ ሳይሆን በብዙ ምሰሶዎች እንመስላታለን:: ምክንያቱም ምሰሶነቷ ለዚህ ገዳም ብቻ አልነበረምና፣ ገድሏም በአንድ ወገን ብቻ አልነበረምና:: ይህ ምሰሶ ሽቱ የተቀባ (ፈተናዋ)፣ መልካም መዓዛ ያለው ዕጣን (ጸሎቷ)፣ የነጋድያን ልዩ ቅመም (የተሰጣት ጸጋና ያተረፈችበት መክሊቷ) ነው:: እኛም ሁላችን እንደ እርሷው ሁሉ፥ መንግሥቱን ወርሰን በጌታችን፣ በቅድስት እናቱ፣ በቅዱሳን መላእክቱ፣ በጻድቃኑና ሰማዕታቱ ዕቅፍ ለመግባት ያበቃን ዘንድ ምኞቴ ነው:: (አሜን ይሁንልን ይደረግልን)::

ለዚህ ገዳም መነኮሳይያትም ሆነ፥ በሌላ ቦታ ላሉ ወዳጆቿ ሁሉ፤ መጽናናትን እንመኛለን:: ኄራኒ በቅዱስ ሲኖዶሱ አባላት ዘንድ ክብርትና የተወደደች እናት ናት:: ነገር ግን በብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ሕመም ምክንያት፤ አብዛኞቹ አገልጋዮች ከእርሱ ጋር ከሃገር ውጪ ስለሆኑ፥ ዛሬ እዚህ አልተገኙም:: አባታችንን በሰላም በጤና ለሃገሩ ያብቃልን:: በእማሆይ የሐኪም ቤት ቆይታ፥ በተደጋጋሚ ስልክ እየደወለ ስለ ጤንነቷ ተከታትሏል:: እኔ ዘንድም ደውሎ፥ «አንተ ራስህ ሄደህ እያትና ያለችበትን ሁኔታ ንገረኝ» ይለኝ ነበር:: ይህ የሚያሳየው፥ እርሷ ለቤተ ክህነቱና ለአባታችን ታላቅ ሥፍራ ያላት እናት መሆኗን ነው::

በዚህ ዕለት እዚህ ሥርዓት ላይ የተገኛችሁትን ሁሉ፤ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ስም ላመሰግናችሁ እወዳለሁ:: አቶ ፋውዚ ሻኽርን ወክሎ ለላከልን፤ ለክቡር ፕሬዚደንት ሞሓመድ ሆስኒ ሙባረክና ለሌሎችም የሚንስትር መስሪያ ቤት ተወካዮች፤ እንዲሁም ለሚገባውና ለሚወጣው ሕዝብ፥ በር አካባቢ ሥርዓት በማበጀት፤ ለተባበራሁን ሁሉ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ:: በረከተ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!

እናታችን ባረፈች በአራተኛው ቀን፤ የዓለም ሕዝብ ሁሉ በረከቷን ያገኝ ዘንድ በገዳሙ ተሰባስበው፥ ድንቅ ተአምራቱን ያደረገላቸውን፥ ሕያው እግዚአብሔርን በአንድነት አመሰገኑ:: ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከል፤ አንድ ቤተሰብ በሞትና በሕይወት መካከል የነበረ ወንድማቸው፣ ዶክተር ያህያ ማላክን ይዘው ወደ ሐኪም ቤት ሊሄዱ ሲሉ፥ ያጋጠማቸው የሕሙማን ማመላለሻ መኪና፤ የእማሆይ ኄራኒን ቅዱስ ሥጋ ከሐኪም ቤት ወደ ገዳሙ ያደረሰው ነበር:: ታማሚውን ደግፈው፥ በቅዱስ ሥጋዋ የተባረከው የሕሙማን ማንቀሳቀሻ አልጋ ላይ ገና ሲያሳርፉት፤ ከሙታን እንደ

ተነሣ ሰው ፈጥኖ ብድግ አለ፣ ሕመሙም ሁሉ ለቀቀው:: ቤተሰቡም «የነቢዩ ኤልሳዕ ቅዱስ ዐፅም፤ የሞተውን ሰው እንዳስነሣ ሁሉ፥ እናታችን ያረፈችበት አልጋም የተባረከ ነውና ወንድማችንን ከሞት አፋፍ መለሰልን» ብለው መስክረዋል::

ከቃለ ምእዳን በኋላ፤ ቅዱስ ሥጋዋን መነኮሳይያቱ ተሸክመው አውጥተው፤ ሌሎች አባቶችም በመቀባበል ጉዞ ሲደረግ፤ እናት መነኮሳይያት፥ ከእነርሱ ጋር ለዘመናት ሰላማዊና የተቀደሰ ሕይወት የኖረችውን እናታቸውንና እኅታቸውን ለመሸኘት፥ ሻማ አብርተው ይከተሉ ነበር:: በ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.፥ በአቡ ሰይፊንና ቅድስት ዴምያና መንበር አጠገብ የተዘጋጀላት ሥፍራ ላይ፤ ሐሙስ ዕለት በ፳፫/፪/፺፱ ሥጋዋን አሳረፉት:: በ፺፰ ዓ.ም.፥ የሕመሟ ዋና ምክንያት የአንጀት ነቀርሳ መሆኑ ከታወቀ በኋላ ነበር፥ ቀደም ተብሎና ልዩ ዝግጅት ተደርጎ፤ በአባ ሩዊስ አስተባባሪነት የቀብሯ ሥፍራ የተዘጋጀው::

ውዷ እናታችን ኄራኒ፦ አንቺ ከዘለዓለማዊ ሕይወት ምንጭ ውኃ እየጠጣ የሚለመልምና የሚያፈራ ዛፍ ነሽ:: ዐይኖችሽ በጉ ወዳለበት ሥፍራ ያማትራሉ፣ ልብሽም ያንኑ ይናፍቃል፣ መሻትሽ ሁሉ አማናዊው በግ ብቻ ነው:: ወደ ሰማያት ተመስጠሽ በዝማሬ እያወደስሽ፥ እውነተኛውን የትሕትናና የቅድስና ፍሬ አፍርተሻል:: የመንፈስ ፍሬዎችሽ (ደቀ መዛሙርትሽ) በሙሉ እግዚአብሔር ለምርጦቹ በሚሰጠው የተለያየ ጸጋ ያሸበረቁ ናቸው:: «እግዚአብሔር ለሚፈሩት ኀይላቸው ነው፥ ቃል ኪዳኑንም ያስታውቃቸዋል» (መዝ.፳፭፥፲፬)::

ውዷ እናታችን በረከትሽ ሁሌም በእኛ አድሮ እደሚኖር ይሰማናል:: በሕይወት ሳለሽ ታደርጊ እንደነበረው ሁሉ፥ አሁንም በየዕለቱና በየሰዓቱ በያለንበት ትጎበኚናለሽ:: በምናስበው ነገርም ሆነ በምንሠራው ሥራ በመንፈስ አልተለየሽንም:: በየበኣታችን አብረሽን ነሽ:: ሰፊውን የዕውቀት አድማስ በዓይናችን ሥር ዘርግተሽልናል:: ሕይወታችን ብርሃናዊ እንዲሆንና የዘለዓለም ደስታ እናገኝ ዘንድ፤ በተሰጠሽ ጸጋ፣ ዐቅምሽ በፈቀደው ሁሉ ረድተሽናል:: አሁንም እየረዳሽን ነው:: «ዜና ገድልሽን ለመጻፍ ስንዘጋጅ፤ ዕውቀትሽ፣ ጸጋዎችሽ፣ የመንፈስ ጥንካሬሽ፣ የገጠሙሽ ፈተናዎች . . . እንኳን ተጽፎ ታስቦ የሚዘለቅ አልሆነም:: ከዚህ የተረዳነው ከታሪክሽ ባሕር ጥቂቷን ጠብታ ብቻ እንደምናቀርብ ነው:: ሆኖም የተቻለንን ያህል ለማሟላት ሞክረናል::

በዓለም ላይ ያሉ ወዳጆቿን ያሸበረ፥ ዜና ዕረፍት፦ ጋዜጠኛ ፊቅጦር ሰላማ «ዋታኒ» በተሰኘው ጋዜጣ፥ ጥቅምት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ክብርን የተጎናጸፈው የገዳማዊቷ እናት ሥርዓተ ቀብር በሚል ርዕስ፤ የአገልግሎቷን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ፋይዳ፣ በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በውጭ፥ በተለያየ አጋጣሚ ባገኛት፤ ሕዝብ ዘንድ ያላትን ሥፍራ፣ ራሷን ዝቅ ስለማድረጓ (ስለማዋረዷ)፣ ስለ ትሕትናዋ፣ ልግስናዋና የአደረጃጀት ችሎታዋ፣ ገዳሙን ምን ያህል እንደለወጠችውና እንዳስፋፋችው፣ እንዲሁም

ገዳማዊውን ሕይወት፥ ወደ ቀደመው ሥርዓት እንዴት እንደ መለሰችውና፤ በእርሷ እናትነት ይመሩ ከነበሩት መነኰሳይያት አብዛኛዎቹ፥ የየገዳማቱ እመምኔት እንደ ሆኑ፤ በመግለጽ አንድ ገጽ ዘገባ አቅርቧል። ዋታኒ ጋዜጣ፥ እናት ኤራኒን አስመልክቶ ለአባቶች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ፥ አንድ አባት የአርጌዋ ካይሮ የበረከት ምንጭ ናት ብሎ ገልጿታል።

በአንድ የውጭ ጋዜጣ ደግሞ፥ ብርሃናዊ ሕይወት በሚል ርዕስ ሥር፥ በዚህ ክፉትና ተንኰል በነገሠበት በ፳፩ኛው መ.ዓ.፤ እንደ እናት ኤራኒ ዐይነት ሰው ግብፅ ላይ ማየት ከተቻለ፥ እርሷ ከዚች ምድር ሳትሆን፥ ከሰማያት የመጣች ናት ቢባል ማጋነን አይሆንም። በዚች ምድር ላይ የነበራት ቆይታ፥ ዓለሙን ከነምናምኑ የሚያስረሳና በጽኑ እምነት፣ በሰላም፣ በደስታ፣ በልግስና፣ በፍቅር የተሸፈነ ከዓለማዊው ምኞት ሁሉ የተጋረደ ነው። በብዙ በሽታ መሰቃየቷ፣ ከመሰቃየትም አልፋ፥ በተደጋጋሚ ጊዜ ከራሱ ከሞት ጋር መፋጠጧ ሁሉ፤ ለእርሷ ቦታ አልነበረውም፣ ጽናቷንም አላነቃወጸባትም። እስከ ዕለተ ዕረፍቷ ድረስ፤ ለገዳሟ መነኰሳይያት ታደርግላቸው የነበረው እንክብካቤ፥ ሩኅሩኅና የተላበሰ ነበር፥ ሲል ጽፏል።

አንድ የፈረንሳይ ጋዜጣም «Décés de Tamav Irénie» በሚል ርዕስ፤ ሥር ሰፋ ያለ ሐተታ ያቀረበ ሲሆን፥ ትርጕሙ ከሞላ ጎደል እንዲህ የሚል ነበር . . . ቅዱስ ሥጋዋን ወዳጆቿ ይሰናበቱ ዘንድ፥ በቅዱስ መርቆሬዎስ ቤተ ክርስቲያን ተቀምጦ ነበር። ጣማፍ ሥጋዋ በሣጥን ውስጥ ሆና፥ ንግግርም እንቅስቃሴም አልነበረውም። ነገር ግን ሥጋዋ ባረፈበት ሁኔታ፤ መስቀሏን በእጆቿ ይዛ፣ ከፈገግታዋ ጋር ላያት ሰው፤ ለጊዜው ዐረፍ ያለች እንጂ ለዘለዓለሙ ያሸለበች አትመስልም ነበር . . .። በእርግጥም ጣማፍ በሕይወት ዘመኗ ገዳሙን እንዳልተለየችው ሁሉ አሁንም አልተለየችውም። በገዳሙ በሌላኛው ወገን አለችልን፤ ጥበቃዋም አይለየንም። እኛም ከምድራዊ ፈተና እንድንድን ዘንድ፥ በጸሎትሽ አሳስቢ ከማለት የተሻለ ቃል የለንም።

ዘመናዊት በረኻዊት እናት፦ (አል-አሕራም ሳምንታዊ ጋዜጣ)፥ ኅዳር ፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ባወጣው እትሙ፥ «A Modem Deseret Mother-ዘመናዊት በረኻዊት እናት» በሚል ርዕስ ሥር፥ ስለ እማሆይ ኤራኒ ሰፊ ዘገባ አቅርቧል። ቀጥሎ ያለው ዝርዝር ዜና፥ ይህ ጋዜጣ በድረ ገጽ ያቀረበው ነው፦

«ጣማፍ» የሚለው ቃል፥ በቅብጥ «እናቴ» ማለት ነው። ጣማፍ ኤራኒ (እናት ኤራኒ)፥ የቅዱስ መርቆሬዎስ የሴቶች ገዳም እመምኔት ነበረች። የተሾመችው ጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ.ም. ነው። በገዳሙ የቅዱስ ጳኵሚዮስን (፪፻፺፪-፫፻፵፮) ቀኖና (የአንድነት ኑሮ ሥርዓት) ያስጀመረች እርሷ ናት። የአፈጻጸሙን ሥርዓት ያገኘችው፤ በዚያው በገዳሙ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ በመነኰሳይያቱ ተዘንግቶ ከቆየ ጽሑፍ ነው። በቅብጥ ቤተ ክርስቲያን፥ ታላቅ ሰማዕት በሆነው በቅዱስ መርቆሬዎስ ስም በተመሠ

ረተው ጥንታዊ ገዳም ውስጥ፤ የሚገኘውን ቤተ ክርስቲያን ያሳነፀችው እርሷ ናት።

እንደዚሁም እመቤታችን በስደቷ ጊዜ አርፋበታለች፥ በሚባልለት በገዳሙ ውስጥ ባለ ሥፍራ ላይም፤ የእመቤታችንን ቤ.ክ. አሳንፃለች። የቅዱስ መርቆሬዎስ ስም በግብፅ ብቻ ሳይሆን፤ በዓለም እንዲታወቅ ያደረገች በመሆኗ ምክንያት፤ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ጋር ትነጻጸራለች። ማለትም፥ ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን፥ ከቅዱስ ሚናስ ጋር ባለው የጠበቀ ወዳጅነትና ግንኙነት አማካይነት፤ በእርሱ ምልጃ ለብዙዎች ተአምራት በመፈጸሙና ለዓለሙም በማሳወቁ ነው። እናት ኤራኒም፥ ቅዱስ መርቆሬዎስና ገቢረ ተአምራቱ፤ በብዙ ሺህዎች ዘንድ እንዲታወቅ አድርጋለች።

ዕረፍቷ ከመሆኑ ከጥቂት ዓመታት በፊት፤ በየሳምንቱ ዐርብ ዕለት፥ ቋሚ ጉባኤያትን ታኪያሂድ ነበር። በእነዚህ ጉባኤያት የተሳተፈና ትምህርቷን ያደመጠ ሁሉ፤ ተስፋና መጽናናትን ሳያገኝ አይመለስም። አንደበተ ርትዕት በመሆኗ፤ ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር እንዲማረኩ አድርጋለች። በዘመኗ የመነኰሳት ቍጥር የመጨመሩ ምሥጢርም ይኸው ነው። አሁን በገዳሙ ውስጥ መቶ መነኰሳይያት የሚገኙ ሲሆን፥ ብዙዎቹ ደግሞ በሌሎች ገዳማት በእመምኔትነት በማገልገል ላይ ናቸው። ልክ እንደ ቅድስት ሲንቅሌጢቃ ሁሉ፤ እናት ኤራኒም ከሃብታም ቤተሰብ ተወልዳለች። ቅድስት ሲንቅሌጢቃና ሌሎች የበረኻ እናቶች፤ በአራተኛውና አምስተኛው መ.ዓ. የገዳማዊ ሕይወት መሠረት የጣሉ ሲሆኑ፤ እንደ አበው መነኰሳት ሁሉ፥ እነርሱም ለብዙዎች መልካም አርኣያ ሆነው አልፈዋል። ትምህርታቸው የሚያተኵረው ንቃት፣ ጸሎት፣ ጾም፣ ጽኑ እምነትና ተጋድሎ፣ የልብ ንጽሕና፣ ድኅነተ ነፍስ . . . ላይ ሲሆን፥ የጣማፍ ኤራኒ ትምህርትም ከዚህ የተለየ አይደለም።

ገዳሙ፥ በእርሷ አነሣሽነትና መሪነት፤ ሴቶች ለምንኵስናና ለብሕትውና ሕይወት ያላቸውን አስተዋጽኦ የሚገልጽና በመጠኑ ጥቆማ የሚያደርግ መጽሐፍ አሳትሟል።[19] የእናታችን ኤራኒ ሕይወትም፤ በዚህ ሁኔታ በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችልና፤ በዘመናችን የታየና የተሰማ ሕያው ምሳሌ ነው። ከ፳፫ ዓመታት በላይ፤ ብዙ በሽታዎችን ተቋቍሞ በምስጋና ሕይወት መኖር መቻል፤ ጥንት የኖሩትን ባሕታውያት እናቶች ሕይወት፥ እንደ ገደል ማሚቶ ያስተጋባል።

ለእርሷ መታሰቢያ በተዘጋጀ ጉባኤ ላይ፤ የአቡ ሰይፊን መነኰሳይያት፥ ብሩህት እናት፣ መልካም መሪና መምህርት፣ ብርሃኑ ለዘለዓለም የማይጠፋ ሻማ ሲሉ አወድሰዋታል። እነርሱም የእርሷ ደቀ መዛሙርት የመሆን ዕድል ስለገጠማቸውና፤ የእርሷ ዐይነት ፋና ወጊና ለግብፅ መነኰሳት ሁሉ ጥሩ አርኣያ የሆነች መነኰሲት፥ ትገኛለች ተብሎ በማይታሰብበት በዚህ ዘመን፤ እርሷን በማግኘታቸው «እግዚአብ

[19] {ይህ «The Virgin Mary & Other Virgins in different ages/Cairo: H.P.P,2000» በሚል ርእስ የታተመውና በአል-አሕራም ጋዜጣ የተጠቀመው መጽሐፍ፥ አሁን እያነበቡት ያለው መጽሐፍ የመጀመሪያው ክፍል ነው።}

ሔር እርሷን እናት አድርጎ ስለሰጠን፤ ዕድለኞችና ደስተኞች ነን። አስተምህሮዋና ያሳለፈችው ሕይወቷ፤ ከዕረፍቷ በኋላም ቢሆን ብርሃን ሆኖ እየመራን ነው። ወደ ፊትም በሰማያት እስክናገኛት ድረስ ይመራናል። በሥጋ ብትለየንም፤ በመንፈስ አብረን ነን» ብለዋል።

<u>ቅድስት ንጽሕት እናታችን፥ ጣማፍ ኄራኒ፦</u> (አል-አሕራም ጋዜጣ) ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.፥ በቅዱሳን መላእክት፣ ሰማዕታትና ጻድቃን ታጅባ ወደ ሰማያት ያረገች፤ ቅድስት፣ ንጽሕት እናታችን ጣማፍ ኄራኒ፥ እመምኔታችን፣ መንገድ ጠቋሚያችን፣ መሪያችን፣ ለገዳማቱም ለዘለዓለም የማይጠፋ መብራታችን ነች። ምድራዊ ግዴታዋን በአግባቡ ተወጥታ ያለፈች ታላቅ እናት ናት። ሊቃነ መላእክቱም ቅዱስ ስሟንና ብርሃናዊ ሕይወቷን፤ በብርሃን መጻፊያ በሰማያት ሰሌዳ ጽፈውላታል።

እጅግ አድርገን የምንወድሽ እናታችን ጣማፍ ሆይ! አንቺ የገዳማችን ጥዑም ዜማ እንደ ነበርሽ ሁሉ፤ አሁንም በጌታችን ፊት ከቅዱሳኑ ጋር በአንድነት ዘለዓለማዊ የምስጋና ዝማሬ ታቀርቢያለሽ። በአንቺ ምስጉን አገልግሎት፤ ገዳማችን በሰማያዊ ሥርዓት እየተመራ ይገኛል። አንቺ የደስታችን ምንጭ፣ ብርታታችንና ላነጋገረሽ ሰው ሁሉ የመንፈስ መጽናኛ ነበርሽ። ከአንቺ ጋር የሆነ ሁሉ፥ ከንጹሕ ልብሽ ጋር የጠለቀ ግንኙነት አለው። ጽኑ መንፈሳዊነትሽና ራስሽን ዝቅ ዝቅ ማድረግሽም፤ በእያንዳንዱ ላይ የሕይወት ለውጥ አምጥቷል። በብሩህ ፈገግታሽ አማካይነት የአምላካችን የእግዚአብሔርን የብርሃን አባትነት አይተዋል። አንቺ ለሁሉ ክፍት የሆነና ሁሉ የሚዘግነው ጥሪት የያዘ ውድና መልካም ሙዳይ ነሽ።

ገዳማትን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ያሳደግሽ፤ በመልካም ሕይወትሽና በጣፋጭ አስተምህሮሽ፤ እኛን መነኮሳትንም ወደ ጥንታዊው ገዳማዊ ሕይወት የመለስሽ፣ ከበረከተኞቹ ግሑሳን ጋር ያስተዋወቅሽ፣ የገዳማቱ ሁሉ መሠረት አንቺ ነሽ። ውዷ እናታችን! አንቺን ስናመሰግንና ለአንቺ ውዳሴ ስናቀርብ፤ በአንቺ ላይ ጸጋውን ያሳደረውንና ሞገስ የሆነሽን፣ አንቺ ወዳለሽበት ደረጃ ሊያደርሰንም ፈቃዱ የሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እያመሰገንን ነው። በዘለዓለማዊው መንግሥቱ ሁላችንንም ያገናኘን! አሜን፥ ብለው ዘግበዋል።

<u>የቅድስቷ ሰርግ፥ በመንግሥተ ሰማያት፦</u> (አል-መሻይር ጋዜጣ) ኅዳር ፲ ቀን ባወጣው እትሙ፥ <u>የቅድስቷ ሰርግ በመንግሥተ ሰማያት</u> በሚል ርዕስ ሥር፥ ስለ ቅድስናዋ ዘርዝሮ ጽፏል። በጽሑፉ ውስጥ ከተሰመረባቸው ቃላት ጥቂቶቹ እንዲህ የሚሉ ነበሩ፦ «. . . ሰላማዊት እናታችን ኄራኒ፥ በጸጥታ ዕረፍት ላይ ሆነች እንጂ አልሞተችም! «ኄራኒ» የሚለው ቃል፥ ወደ ዕርዕ ቋንቋ ሲመለስ «ሰላም» ማለት ነው። ብሩህ ልቧ የሌሎችን ልብ የመሳብ ኃይል አለው። . . . ልቧ ምቱን ቢያቆምም፤ የጸሎቷ በረከት ግን ሁሌም ከእኛ ጋር ይኖራል። . . .»።

እንዲሁም ስለ ሀብተ ትንቢቷ በገለጹበት ጽሑፍ ላይ፤ በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ሄልዮፖሊስ በሚገኘው የቅ.ጊ.ቤ.ክ. ስለ ተከሰተው አደጋ ለምሳሌ ጠቅሰዋል። አደጋው በደረሰ ጊዜ፤ ጣማፍ እዚያ የነበረች ሲሆን፥ በዚህ አደጋ ምክንያት ሕይወታቸውን ያለፉ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ልጆች፤ በራሳቸው ላይ የክብር አክሊል እንደተደረገላቸውና ነፍሳቸው በሰላም እንዳረገች በማየቷ፥ በቦታው ለነበሩት የኃዘን ተካፋዮች ሁሉ ነግራ አጽናንታቸዋለች። እንዲሁም በእርሷ ጸሎት አማካይነት፤ ብዙ ሕሙማን ተፈውሰው በረከተ እግዚአብሔርን አግኝተዋል፥ ብሏል።

ለ፴፭ ዐመታት የሚያውቃት አንድ የቅብጥ ቄስ፥ ጋዜጠኞች ባደረጉለት ቃለ መጠይቅ፥ በዓረፈች በአራተኛው ቀን የገጠመውን እንዲህ መሥክሯል፦ ቅዳሴ እየቀደስሁ ነበር። ማዕጠንቴን ይዤ በዕረፍት ስላሉ ሰዎች የሚደረገውን ጸሎት ሳደርስ፥ ልክ «አቤቱ ጌታዬ ሆይ! እናታችንን አገልጋይህ ጣማፍ ኄራኒን በመንግሥትህ አስባት» እንዳልሁ፤ ወዲያው መጣችና በራእይ ፫፥፳፩ የተጻፈውን "እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ፥ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደ ተቀመጥሁ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ" የሚለውን ጥቅስ ትርጕም አስረዳችኝ።

በገድሏ ና በቅድስና ሥራዋ ባገኘችው ክብር፤ ከጌታችን ቀኝ ተቀምጣ ነበር የተገለጠችልኝ። በሕይወት ሳለች በኃዘኗም በደስታዋም ጊዜ አይቻታለሁ። አሁን ደግሞ፥ በሰማያት በእግዚአብሔር ሞገስ ደምቃና እያበራች ተመለከትኋት። እንዲሁም በሕይወት በነበረች ጊዜ፥ ከአቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ቀጥሎ ስለሚሾመው ፓትርያርክ፤ ስም ለማስባሰብ በዝግጅት ላይ ሳለን፤ ስለ አቡነ ሲኖዳ ፫ኛ ሹመት ቀደም አድርጋ ነግራናለች።

ከአቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ጋር ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ግንኙነት አላት። በተሰጣቸው ጸጋ፥ በሁለቱ አማካይነት የተፈጸሙት የተአምራት ብዛት ተቈጥረው አያልቁም። ልክ እንደ አቡነ ቄርሎስ ሁሉ፥ እርሷም በሓኪምና በሕክምና ሳይንስ ዘንድ አለቀላቸው የተባሉትን በጸሎቷ ፈውሳለች። እጅግ ብዙዎችንም በንስሐ እንዲመለሱና ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀርቡ አድርጋለች።

በአካል ያዩዋት፣ በዝና የሚያውቋትና በሕልም ተገልጣ በጸሎቷ የረዳቻቸው፤ በግብፅና በውጪ ያሉ ሁሉ፤ በተለያዩ ድረ ገጾች፥ በየቋንቋቸው እንዲህ ሲሉ ስለ እርሷ በመጻፍ አወድሰዋታል፦

- ✝ ርኅሩኅቷ እናቴ! በአካል በዓይኔ ባላይሽም የመልካም ሥራሽን መዓዛ ለማሽተት ታድያለሁ።
- ✝ ርኅሩኅነትሽና የጸሎትሽ ኀይል፥ የመንፈስ ቅዱስን ሙቀት ያስጣል፣ ደካማውን ያበረታል፣ የታመመውን ይፈውሳል።
- ✝ ደግ እናቴ! ለሁሉ ትሰጫለሽ፤ ዋጋሽን ግን ከሰው አትጠብቂም። ርኅሩኅት እናቴ

ቡርክት ነሽ።

† የጸሎትሽ ኀይል፥ ድሃውን የመንፈስ ሀብታም፣ ኀጥኡን ናዛዚ ያደርጋል።

† እናቴ! ፍቅርሽ ብዙዎችን ስቧል፣ ወደ መለኮታዊው ፍቅርም አቅርቧል። የሰማይ ሙሽሪት የመንግሥቱም ተጠሪ ነሽ።

† አንቺ ሕያው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ዕንቊኣችንም ነሽ።

† አንቺ በምድር ሳለሽ በሰማያት የኖርሽ፥ ሰላማዊት ሙሽራ ነሽ።

† አንቺ የዘመናችን ግብፃዊት ቅድስት ነሽ።

† መመረጥሽ ከሰማያት የሆነ መነኩሲት፣ በሰማያት ተጨማሪ አማላጃችን፣ የቅድስናና የርኅሩኅና ምሳሌ ነሽ።

† ንጽሕት ሙሽራ ሆነሽ ለመገኘት ስትይ፤ ትልቅ መስቀል በጫንቃሽ ያኖርሽ፥ የፍቅር፣ የልግስና፣ ራስን የማዋረድ (የመናቅ)፣ የቅድስናና የንጽሕና ጣዕመ ዜማ፣ መልካም መዓዛ ያለው የተመረጠ ዕጣን ነሽ።

በዚህ ዐይነት አገላለጽ፤ በመጽሔት፣ በጋዜጣ፣ በድረ ገጽ፣ በቴሌግራምና፤ እንዲሁም በአካል እየተገኙ፥ በገዳሙ በተዘጋጀ ትልቅ መዝገብ ላይ፤ አስተያየታቸውን በመስጠት፤ ስለ እናታችን ኄራኒ በቃል ለመግለጽ የሚቻለውን ያህል ተናግረዋል። ይህ ሁሉ ግን፥ የእርሷን መልካም ሥራ፣ ቅድስናዋን፣ ደግነቷን . . . ጠቅልሎ ይዟል ወይም ገልጿል ማለት አይደለም። ያደረግነው ሙከራ ከብዙው እጅግ ጥቂቱን (ዐባይን በጭልፋ የመሞከር ያኽል) ነው።

ካይሮ ከተማ በሚገኙ፥ አንድ የአቡ ሰይፊን ገዳም ውስጥ፤ ጸሎት እያደረሰ ያለ ካህን ነበረ። ከበድ ያለ ችግር ገጥሞት፥ ገንዘብ በጣም ያስፈልገው ነበር። ይህን ችግሩን ግን በጸሎት ከማሳሰብ ሌላ ለማንም አልነገረም። ጸሎቱን አብቅቶ ከቤተ ክርስቲያን ከመውጣቱ በፊት፥ አንዲት መነኩሲት መጥታ፤ ከእማሆይ ኄራኒ ነው የተላከልህ ብላ፤ በፖስታ የታሸገ ብር ሰጠችው። ፖስታውን ሲከፍት፥ ሁለት ሺህ የግብፅ ፓውንድ በውስጡ አገኘ። ወደ ገዳማችን መጥቶ፤ «እኔ አንቺን አላውቅሽም። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በገለጠልሽ ይህንን አደረግሽልኝ» ብሎ፥ ባዘጋጀነው መዝገብ ላይ፤ የምስክርነት ቃሉን ጻፈ።

ለማጠቃለያ ይሆነን ዘንድ፥ ከሊባኖስ የደረሰንን የቴሌግራም መልክት እነሆ፦ እማሆይ ኄራኒ ከማረፏ ጥቂት ጊዜያት ቀደም ብሎ፥ አንዲት ሴት ጣማፍን ለማነጋገር፤ ከሊባኖስ ወደ ገዳማችን ስልክ እየደጋገመች ትደውል ነበር። ነገር ግን ጣማፍ ሕክምና ላይ በመሆኗ ምክንያት የሴትየዋ ጥሪ መልስ አላገኘም። ደዋይዋ ሴት፥ ስለ እማሆይ ሕመም ስላልሰማች፤ ለምንድነው ስልኳን የማታነሣው? እያለች ታዝን ነበር። ከዚያ የሆነውን እንዲህ ገልጻዋለች፦

«በስልክ ላገኛት ባለመቻሌ እያዘንሁ ሳለ፥ እማሆይ በሕልሜ ስለ ተገለጠችልኝ። «ሰው ስልክ ሲደውልልሽ መልስ አትሰጪም? እንደዚህ ይደረጋል እንዴ?» አልኋት። የተወደደች ጣማፍ ኄራኒም፤ አንድ የስልክ ማናገሪያ የመሰለ ትንሽ ዕቃ ሰጠችኝና፤ ከአሁን ብኋላ ስትፈልጊኝ በዚህ ደውዪ። ጥሪውን፥ ቀጥታ ወደ ሰማያት ያስተላልፍልሻል አለችኝ። ከዚያ ወደ ሰማይ ራሴን ቀና ሳደርግ፤ ሰማያት ተከፍተው እጅግ ደስ የሚያሰኙ ነገሮች በማየቴ፤ ፎቶ ለማንሣት ካሜራዬን ላመጣ ተነሥቼ ሄድሁ። ስመለስ ግን ሁሉም ተሰውሮ ቆየኝ። ከጥቂት ቀናት በኋላም፣ ዕረፍቷን ሰማሁ»።

ምዕራፍ ስምንት

ገዳማዊ ሕይወት፥ በፍኖተ ቅዱሳን።

«ራሳችሁን ያስገዛችሁለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ የልባችሁን መሻት ያከናውንላችኋል»[20]

«እኔ መረጥኋችሁ እንጂ፥ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ የምትለምኑትን . . .» እንዲል፥ በፈጣሪዋ የተመረጠች ጣማፍ ኄራኒ፥ በጾም፣ በጸሎትና በአገልግሎት የተጋች መነኩሲት መሆኗን፥ ባለፉት ጽሑፎች ጠቅሰናል (ዮሐ.፲፭፥፲፮)። የመንፈሳዊን ሕይወት ጥቅምና መዳረሻ ምዕራፉን በደንብ ተረድታለችና፥ ገዳማውያኑም በዚህ ትጋት መጓዝ ይችሉ ዘንድ፣ ማጠንከሪያ በሆነው በማኅበራዊ ሕይወትም፥ ሁሉም ይሳተፉ ዘንድ፣ የቻለችውን ሁሉ አድርጋለች። ድርጊቷ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ በመሆኑ፥ ፍሬውም ያማረ ነው። ለእያንዳንዱ ለለገሰችው የፍቅር አገልግሎት፤ በአጠፌታው ዋጋዋን በሰማያት ተቀብላለች። ጣማፍ ለገዳሙ ያበረከተችውን አገልግሎት ለመቃኘት ይረዳን ዘንድ፤ ስለ ቀድሞው የአ.ሰ.ሴ.ገ. ታሪክ በጥቂቱ እናስተዋውቃችኋለን። በእርግጥ ጥንታዊውን ይዞታ በማደስና በማሟላት ረገድ የመጀመሪያው ተሳታፊ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፭ኛ[21] ነው። በጣማፍ እንደበት የተነገረንን ታሪክ እንዳለ አቅርበነዋል፦

ታሪክ እንዳቆየልን መረጃ፥ የታላቁ ሰማዕት የአ.ሰ.ሴ.ገ. ጥንቱ ፬፻ ዓ.ም. ነው። አሁን ለዕድሳት በተደረገው ቁፋሮ፥ በብረት ላይ በእንግሊዝኛ «The Convent of Girls» *በዓረብኛ ደግሞ* «Dayr al-Banat» *የሚል ጽሑፍ ታትሞበት ተገኝቷል። «ዲር አል-በናት» ትርጕሙ «የልጃገረዶች ገዳም» የሚል ነው። በዚህ መረጃ የገዳሙ የቀድሞ ስም «የልጃገረዶች ገዳም» መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ገዳሙ የሚገኘው በናይል*

[20] ቅዱስ ጳኵሚየስ የአንድነት ኑሮ መሥራች።

[21] አቡነ ቄርሎስ ፭ኛ፥ (ዘመነ ፕትርክናው ፲፰፻፷፮-፲፱፻፲፱) በመንበረ ማርቆስ ከተቀመጡት ፻፲፪ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ነው። ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን በማደስና በማስፋፋት ትልቅ አገልግሎት ሰጥቷል።